# ስለ ወንጀል ቅጣት ወለል አወሳሰንና አፈጻጸም

**ጥናቱን ያከናወኑ ባለሙያዎች፡-**

ኃይለሚካኤል መላኩ
የትናየት ደሳለኝ
መስፍን እሸቱ
ሄርሜላ ጌታቸው

**በጥናቱ የቀረበ ምክረ ሀሳብ**

በመንግስትና በህብረተሰቡ ላይ ከፍተኛ ጉዳት በሚያደርሱ ወንጀሎች አንጻር ከወለል ወርዶ ቅጣት የመወሰን አሰራርን ለማስቀረት የሚያስችል የአስገዳጅ ዝቅተኛ ቅጣት (mandatory minimum sentence) ሥርዓት መዘርጋት ፡፡

በዚህም መሰረት ከሚያደርሱት ከፍተኛ ጉዳት አንጻር በልዩ ሁኔታ እንዲታዩ የተደረጉት በወንጀል ፍትህ ፖሊሲው ቅድሚያ ትኩረት እንደሚሰጣቸው የተገለጹት ወንጀሎች ሲሆኑ በተጨማሪም የቅጣት ወለላቸው አስርና ከአስር ዓመት በላይ የሆነ ከባድ ወንጀሎች እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ቀጥሎ የተዘረዘሩት ወንጀሎች መፈጸማቸው ከተረጋገጠ በወንጀለኛው ላይ ሊወሰን የሚገባው ቅጣት በወንጀል ህጉ ከተመለከተው ዝቅተኛ ቅጣት (ወለል) ያነሰ ሊሆን አይችልም፡፡ ሆኖም ተጠርጣሪው በፈፀመው ድርጊት የተፀፀተና ስለወንጀሉ መረጃ በመስጠት የፍርድ ሂደቱን የረዳ እንደሆነ ወይም ከዓቃቤ ህጉ ጋር ከተደራደረ በዐቃቤ ህግ ጥያቄ መነሻነት ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን ሊያቀልለት ይችላል፡፡

ሀ. የወንጀል ሕግ

**1. በሕገ መንግሥታዊ ሥርዓትና በአገር የውስጥ ደህንነት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች**

(አንቀጽ238 (2) ፣ 240 (1) ፣ (2)፣ 241፣249 (2)፣

**2.በመንግሥት ሥራ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች**

አንቀጽ(407(3)፣408(3)፣411(3)፣413(3)፣414 (3)፣415 (3)

**3. በሰው ሕይወት፣ አካልና ጤንነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች**

(አንቀጽ 539(1) ፣ (2) ፣573 (3)

**4. በሰው ነጻነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች**

(590(2) (ሠ)፣596(3)፣597፣

**5.በመልካም ጠባይና በቤተዘመድ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች**

(አንቀጽ620(3)፣(4)፣626(5)፣627(1)፣(4)(ሀ)፣(5)፣631(1)(ለ)፣(4(ሀ)፣(5)

**ለ.የፀረሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር 652/2001 ዓ.ም.**

**6. ሽብርተኝነት** (አንቀጽ 3-7)

ሐ. በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር 657/2002 ዓ.ም.

7. በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት

አንቀጽ16. ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት፣